# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


## የኢትዮጵያን ህዝብ አደንቁሮ ለመግዛት ህወሀት/ኢህአዴግ የሚያካሂደውን አሳፋሪ ተግባር ሁሉ ሸንጎ አጥብቆ ያወግዛል።

ጥቅምት 18፣ 2007 (ኦክቶበር 28፣ 2014)

በትላንቱ እለት በአዲስ አባባ ውስጥ የሚገኘው የከፍተኛ ፍርድ ቤት በታዋቂው የኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኛ በአቶ ተምሰገን ደሳለኝ ላይ የሶስት አመት ጽኑ እስራት እንደፈረደበት ተገልጿል። አቶ ተመሰገን ለክስ የተዳረገውና ለዚሁ ህገ ገምድል ብይን ያበቃው በተለያየ ጊዜ ያቀረባቸውን ተወዳጅ ጽሁፎቹን እንደ ፈለጉ በመተርጎም "ህዝብ አነሳስቷል የሀሰት ዜና አሰራጭቷል" በሚሉ ተልካሻ የፈጠራ ምክንያቶች ነው።፡

ህወሀት/ኢህአዴግ በሀገሪቱ ህዝብ ላይ የሚፈጽመውን መጠነ ሰፊና ዘግናኝ ግፍ፤ ንቅዘት በስልጣን መባለግና፣ ዘረኛ ፖሊሲ ከህዝብ እይታ ለመደበቅ የማያደርገው ሙከራ የለም ። ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ የሚፈራው በመተክልና በእውነት ላይ የተመረኮዘ፣ ሀሳብን ለህዝብ የሚያሰራጭ ሚዲያንና በዚህ ተግባር ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችንና ተቋማትን ነው።

የመናገር፣ የመጻፍና ሃሳብን በነጻ የመግለጽን መብት አከብራለሁ ብሎ በህገመንግስቱ ውስጥ ጽፎ በየወቅቱ የሚለፍፈው የህወሀት/ኢህአዴግ ስርአት እንዲህ አይነት አይን ያወጣ የፈጠራ ክስ መስርቶ አቶ ተመሰገንን በሶስት አመት እስራት መቅጣቱ፣ ለ23 አመታት የታየውንና ለተደጋጋሚ አመታትም ከአፍሪካ መንግስታት ሁሉ "የነጻ ፕሬስ ቀንደኛ ጠላት" የሚል ስያሜ ያተረፈለትን ጸረ ዴሞክራሲያዊ ተግባሩን አጥብቆ እንደ ቀጠለበት አንድ ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ፣ በአቶ ተመስገን ደሳለኝ ላይ የተወሰነውን የግፍ ፍርድ እንዲሁም በቀጣይነት የኢትዮጵያን ህዝብ አደንቁሮ ለመግዛት ህወሀት/ኢህአዴግን የሚያካሂደውን አሳፋሪ ተግባር ሁሉ አጥብቆ ያወግዛል።

ይህን የግፍ ስርአት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ አሽቀንጥሮ ለመጣል ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ የተባባረ ትግሉን አጠንክሮ እንዲቀጥል ጥሪያችንን በድጋሚ እናስተላልፋለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ


Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com